# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 12 መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## የግብርናና ገጠር ልማት በኢትዮጵያ የኢዜማ ፖሊሲ አቅጣጫ



# የዴሞክራሲ ተቋማት እና ባህል ግንባታ የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው

ዴሞክራሲ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ የፓለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች የሚሆኑበት፤ ይህንን ሥልጣን በተሟላ መረጃ ተመስርተው በነፃነት በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት በተግባር የሚያውሉበት ሥርዓት ነው።

ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ መስፈን መሟላት ያለባቸው በርካታ ተቋማዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም የሰብዓዊ መብቶች መከበር፤ የአብላጫዎች መሪነትና የውህዳን ብዙኃን የመሆን መብት መረጋገጥ፤ የፓለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት መደራጀትና መንቀሳቀስ፤ የነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ የፓለቲካ ፉክክርና ምርጫ መኖር፤ የገለልተኛና ቀልጣፋ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም መኖር፤ የጦር ሠራዊቱ በሕዝብ በተመረጠ ሲቪል አስተዳደር ስር መሆን፤ በኃላፊነት የሚንቀሳቀስ ነፃ ፕሬስና ሚዲያ መኖር፤ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ያለው የአስተዳደር መዋቅርና የመንግሥት ሥርዓት በየደረጃው መዘርጋት፤ በህግ የተገደበ ስልጣን ያለው የሕግ አውጭ አካል መኖር፤ ከፓለቲካ ነፃ  የሆነ የፍትህና የፍርድ ሥርዓት መስፈን ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እያንዳንንዱ ተቋም በሕግ፣ ተቀባይነት ባለው አሠራር እና ችሎታ ባላቸው ሰዎች መመራት ይኖርበታል፤ እያንዳንዱ ተቋም ከሕግ በተጨማሪ ተቋማዊ ባህል ይፈልጋል።

ከላይ የተዘረዘሩት ተቋማትና ተቋማቱ የሚፈልጉት ዓይነት ባህል በአጭር ጊዜ ተገንብተው የሚጠናቀቁ አለመሆኑ፤ እንዲያውም የተቋማትና ባህል ግንባታ የማያቋርጥ ፍፃሜ የሌለው ሥራ መሆኑ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ያምናል። ይሁን እንጂ ወደፊት ጠንካራ ተቋማትና ለተቋማቱ ተስማሚ የሆነ ባህል እንዲኖሩን የተቋማቱ ግንባታ ሲጀመር የሚደረጉ ተግባራት ወሳኝ ናቸው። ተቋማት ከመጀመሪያው በጥሩ መሠረት ላይ መቆማቸው ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ የተቋማት ግንባታ ባለሙያዎች የሚስማሙበት ሀቅ ነው።

በሀገራችን የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ መሠረት መጣል የተጀመረው አሁን ነው ብሎ ኢዜማ ያምናል። በዚህም መሠረት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ የሚኖርበትም አሁን ነው።

የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ መሠረት ሲጣል ባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ለተቋማት ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለው ኢዜማ ያምናል። በዚህም ምክንያት የተቋማት ግንባታ የመንግሥት ወይም የተቋማቱ ብቻ ኃላፊነት ተደርጎ እንዳይወሰድ ኢዜማ ያሳስባል።

የዴሞክራሲ ተቋማት የሚገነቡት ለረዥም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው ነው፤ በግንባታቸውም ኢትዮጵያውያን በተደራጀ መንገድ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ ረገድ እያደረገ ያለው ተግባር የሚያበረታታ ነው፤ ይህ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ኢዜማ ያሳስባል።

የዴሞክራሲ ተቋማት እና ባህል ግንባታ ለመንግሥት ብቻ የምንተወዉ ሳይሆን የዜጎች ሁሉ የጋራ ኃላፊነት ነው። በዚህም ምክንያት ዜጎች በፓለቲካ ፓርቲ፣ በሙያ ማኅበራት ወይም በሌላ የሲቪል አደረጃጀት ተደራጅተው ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ኢዜማ ጥሪ ያቀርባል።

# ኢዜማ አዲስ አበባ ለሚገኙ ሴት አባላቶቹ ያዘገጀው ተከታታይ ሥልጠና ተጠናቀቀ

መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ በሁሉም ወረዳዎች ለሚገኙ ሴት አባላት በኢዜማ ሴቶች ጉዳይ የአቅም ግንባታ ኮሚቴ በኩል የተዘጋጀው ተከታታይ ሥልጠና እሁድ መስከረም 18 ቀን 2012 ዓ.ም ተጠናቀቀ፡፡ ሥልጠናው በተለያዩ ዐበይትና ንዑስ ክፍል የተዘጋጀ ሲሆን የኢዜማ ሀገራዊና ታሪካዊ ፋይዳ ምንድን ነው? የኢዜማ መርሆች ምንድን ናቸው? የኢዜማ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብና ስትራቴጂ እና የኢዜማ የፖለቲካ ፍልስፍና መሠረታዊ ሃሳቦች ምን ምን ናቸው? የዜግነት ፖለቲካ ማለት ምን ማለት ነው? የኢዜማ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ሕገ ደንብና አሠራር እንዲሁም ኢዜማዊ ባህል እንዴት ሊገነባና ሊዳብር ይችላል? የሚሉ ርዕሶት በአራት የተለያዩ ቀኖች በተሰጠው ሥልጠና ላይ የተካተቱ ነበሩ፡፡

እሁድ እለት በተሰጠው ሥልጠና ወቅት ሠልጣኞቹ በቡድን በመሆን ሥልጠናው የሸፈናቸው ርዕሶች ላይ ሰፋ ያለ ውይይት አድርገዋል፡፡

የኢዜማ ሴት አባላት «ስለኢዜማ በደንብ አውቀን ገለጻ ማድረግ የሚያስችለን እውቀት እንዲኖረን እንፈልጋለን፡፡» ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው ከሐምሌ 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 18 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ በየአስራ አምስት ቀኑ ሥልጠናው ተዘጋጅቶ መሰጠቱን የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ የአቅም ግንባታ ኃላፊ ቅድስት ግርማ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

ኃላፊዋ እንደገለጹት ከሥልጠናው በኋላ በቡድን ሆኖ ውይይት መደረጉ ገንቢ የሆኑ ሃሳቦች በሠልጣኝ አባላቶች እንዲነሱ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በዓይነቱ የመጀመሪያው የሆነው ይህ ሥልጠና የተዘጋጀው በአዲስ አበባ ላሉ አባላቶች ቢሆንም ወደፊት ወደ ተለያዩ የሀገራችን ቦታዎች በመሄድ ተመሳሳይ ሥልጠና እንደሚሰጥ ጨምረው ያሳወቁት ኃላፊዋ «ኢዜማ ውስጥ ሰፊ እውቀት ያላቸው ሥልጠና መስጠት የሚችሉ አመራሮች አሉ፤ አሁን እየተሠራ ያለው ሌሎችን የማብቃት ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡» ብለዋል፡፡

## አድራሻ


ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)


መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የግብርናና ገጠር ልማት በኢትዮጵያ የኢዜማ ፖሊሲ አቅጣጫ

## መግቢያ

የሀገራችን ኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ በገጠር የሚኖርና የኑሮ መሠረቱም በግብርና ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በግብርና ሥራ የተሰማራው አብዛኛው ገበሬ በዝናብ ላይ የተመሠረተ ግብርና የሚያካሄድና የተሻሻሉ የግብርና ግብዓቶችን በስፋት የማይጠቀም ስለሆነ ከሰብልና እንሰሳት ልማቱ የሚገኘው ምርትና ምርታማነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በየዓመቱ ከ10 ከመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ በዕለት የእህል እርዳታ ላይ ጥገኛ ሆኖ ይገኛል፡፡

የእንስሳት ሀብት ልማት ንዑስ ዘርፍም ያልተሻሻሉ ዝርያዎችን የሚጠቀም፣ በቂና በጥራት የሚቀርብ መኖ የሌለበትና የእንስሳት ጤና አገልግሎቱም የተዳከመ በመሆኑ ከዘርፉ ሊገኝ የሚገባው ምርትና ገቢ በበቂ እየተገኘ አይደለም፡፡

የሰውና የእንስሳት ቁጥሩም በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ የግብርና ምርት ፍላጎቱን ለማሟላት ገበሬው የደንና የግጦሽ መሬቶችን በመመንጠር ለእርሻ አውሏቸዋል፡፡ የደን ምንጣሮው፣ የአፈር በዝናብ መታጠብ፣ የአፈር ብክለትና የተፈጥሮ ሀብቶችን መመናመን በማስከተሉ የአፈር ለምነት እየቀነሰ፣ የዝናብ ስርጭትና ብዛት እየተዛባ መጥቶ በርካታ የሀገራችን አካባቢዎች በድርቅ ተመተዋል፡፡

የተፈጥሮ ሀብትን ተንከባክቦ ለዘላቂ ልማት ለማዋል አግባብነት ያላቸው የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ሕዝቡንና የተማረውን ሰው ባሳተፈ ሁኔታ ተቀርጸው ሥራ ላይ ባለመዋላቸው፣ አልፎ አልፎ ጥሩ የተባሉ የፖሊሲ ሰነዶች ቢወጡም በአግባቡ በየደረጃው ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ወደ ተግባር ባለመግባታቸው የግብርናው ዘርፍ ችግርን አልፈታም፡፡

የግብርና ሥራ ከመሬት የባለቤትና የመጠቀም መብት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ገበሬው በመሬቱ ላይ ለረጅም ጊዜ ሀብቱን አፍስሶ ውጤት ከሚያመጡ ሥራዎች ይልቅ ጊዜያዊና ዘለቄታዊነት በሌላቸው የግብርና ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር በመደረጉ ለምርት አለማደግና ለተፈጥሮ ሀብቱ መመናመን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በእነዚህና ሌሎች የፖሊሲ ችግሮች የተተበተበው ግብርና እያደገ የመጣው ሕዝብ ተፈላጊውን የሥነ ምግብና የገቢ ፍላጐት ማሟላት አቅቶት ከውጭ ሀገር በሚመጣ የምግብ እርዳታ ላይ ጥገኛ ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሀገራችን ሊመረቱ በሚችሉ ምርቶች ማለትም ስንዴ፣ ጥጥ፣ ዘይት፣ ወተትና የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችን ከውጭ ሀገር በማስገባት በውጭ ሀገር ገንዘብ ጥሪት ላይ ጫና ተፈጥሯል፡፡

ይህ የኢዜማ የግብርናና የገጠር ልማት የፖሊሲ አቅጣጫ የሚያተኩረውም ኢትዮጵያ ሀገራችን እንዴትና ምን በማድረግ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅሙ ጊዜ ከተጋረጠባት የምግብ እጥረት ተላቃ የምግብ ዋስትናዋን በማረጋገጥና የገበሬውን ገቢ በመጨመር የግብርናና ገጠር ልማት ለውጡን ማፋጠን ይቻላል በሚሉት ሃሳቦች ላይ ነው፡፡

## የግብርና ልማት ዘርፍ ፋይዳና ተያያዥ ችግሮች

ግብርና ለአጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚ 34.9% አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ 85 በመቶ ሕዝብ የገቢ እና የምግብ ምንጭ፣ 80 በመቶ የማያንስ ከውጭ ንግድ የሚገኘውን ገቢ የሚሸፈንና 70 በመቶ የሀገር ሀብት የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ግብዓቶችን እንደሚሸፍን ይታወቃል፡፡ ግብርና ሀገራችን ኢትዮጵያ ለምታስበው የኢኮኖሚ እድገትና ሽግግር (Economic growth & Transition) ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል፡፡ እንዲሁም ሀገሪቱ ባላት የተፈጥሮ ሀብት ተነጻጻሪ ጥቅም (Comparative advantage) ያላት በመሆኑ ግብርናን ለማዘመን በአግባቡ የተፈጥሮ ሀብቶቿን መጠቀም ከቻለች ዘላቂነት ያለው ልማት ለማካሄድ የተመቻቸ ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡

ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገትና ሽግግር የጀርባ አጥንት የመሆኑን ያህል በተገቢው የእድገት ደረጃ ላይ የማይገኝና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ዘርፍ ነው፡፡ ይህም በብዙ መለኪያዎች ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና በአብዛኛው በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆነ፣ የተሻሻሉ (ዘመናዊ) ግብዓቶችን የማይጠቀም፣ ኋላቀር የእርሻ ዘዴዎች የሚጠቀም፣ በከፍተኛ ደረጃ የተፈጥሮ ሀብቶቹን ያመናመነና ለከፍተኛ የተፈጥሮ አየር መዛባት የተጋለጠ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በዘርፉ ላይ የሚደረገው መዋለ ንዋይ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

የዘርፉ መገለጫ ከሆኑት ተግዳሮቶች መካከል አንዱ አነስተኛና የተበጣጠሰ የመሬት ይዞታ ለተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም አመቺ ካለመሆኑም ባሻገር ዝቅተኛ የሰው ኃይል ምርታማነት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ትክክለኛ የመሬት ፖሊሲ ተግባራዊ ባለመሆኑ የተነሳ የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ለዘርፉ የወጡ ፖሊሲዎች በተግባር ገበያ ተኮር ያለመሆናቸውና በአብዛኛው በመንግሥት ቁጥጥር ስር የዋሉና የግል ሴክተሩን ያገለሉ በመሆናቸው ዘርፉ በተፈለገው ፍጥነት ማደግ እንዳይችል አድርገውታል፡፡ ዘርፉ እስካሁን ባለው ሁኔታ በከፍተኛ መሠረተ ልማትና በገበያ ትስስር እጦት የሚሠቃይ ከመሆኑም ባሻገር በደካማ ተቋማት አደረጃጀትና የሰው ኃይል ምደባ፣ ሙያን ያላማከለ የፓርቲ ጣልቃ ገብነት የተነሳ የሚፈለገውን እገዛ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ዘርፉን ለማዘመን ቁልፍ ግብዓት የሆኑት እንደ ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና የትምህርት ሥርዓት በአግባቡ ተቀናጅተው የዘርፉን ችግር ሊፈቱ አልቻሉም፡፡

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየታየ ያለው የሕዝብ ቁጥር ምጣኔ ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ የተነሳ በተለይ 73 በመቶ የሆነው ወጣቱ ትውልድ በሥራ አጥነትና መሬት አልባ በመሆን እየተቸገረ ይገኛል፡፡ በዚህም የተነሳ ወጣቱ በቤተሰቡ ላይ ጥገኛ ሆኗል፤ ለስደት ተዳርጓል፤

እንዲሁም የአጉል ሱሶች ተጠቂ ሆኗል፡፡ ኢትዮጵያ ባላት የቀንድ ከብት ሀብት ብዛት “ከአፍሪካ 1ኛ ከዓለም አስረኛ” ብትሆንም ንዑስ ዘርፉ በችግር የተተበተበ ስለሆነና ከፍተኛ የከብት ቁጥር መኖሩ ለተፈጥሮ ሀብታችን መመናመን የራሱን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

## ካለፉ ጥረቶች የሚገኝ ትምህርት

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለፉት ዘመናት ግብርና መር ኢንዱስትሪያላይዜሽን (ADLI) ፖሊሲና ስትራቴጂ አውጥቶ ሲንቀሳቀስ እንደነበረና ይህንንም በተለያዩ የአምስት ዓመት ፕሮግራሞች ነድፎ (SDPRP1, 2 & GTP1, 2) ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም ከንውን በዘርፉ መጠነኛ እድገት የታየ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ይሁን እንጂ የችግሩ ስፋት ከተገኘው ውጤት አንጻር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጉድለት የታየበት ነው፡ ፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሱ ዋና ዋና ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- እስካሁን የወጡ የዘርፉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በየደረጃው ያሉ ባለ ድርሻ አካላትን ያላሳተፉ፣ በጥልቅ የእውቀት ትንታኔ ላይ መሠረት ያላደረጉና አፈጻጸማቸውም ከላይ ወደ ታች በግዳጅ የተተገበሩ በመሆናቸው እና ፖሊሲዎቹም ለረዥም ጊዜ ከሁኔታዎች መቀያየር ጋር አብሮ የማይሄዱ፣ የማይገመገሙና የማይከለሱ መሆናቸው፤
- መንግሥት ለግብርና ዋና መሠረት ብሎ ሁለት የምርት ኃይሎች ማለትም መሬትና የሰው ኃይልን የጠቀሰ ቢሆንም በተለይ መሬት በመንግሥት ባለቤትነት ብቻ የተያዘ እና ገበሬውን በወሳኝነት ከመሬት ባለቤትነት ውጭ ያደረገ በመሆኑ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና በዘላቂ ኢንቨስትመንት እንዳይሳተፍ አካባቢውን በመጠበቅ ምርትና ምርታማነቱን ከፍ እንዳያደርግ ማነቆ ሆኗል፤
- በአጠቃላይ ምርትና ምርታማነቱ ከዘርፉ ከሚጠበቀው በታች በመሆኑ ሕዝቡን በምግብና በገቢ ራሱን እንዳይችል አልፎ ተርፎም ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ባለመቻሉ በየዓመቱ መንግሥት በእርዳታና በግዥ ምግብ ከውጭ እንዲያስገባ ተገዷል፤
- በማንኛውም ጤናማ ኢኮኖሚ የግል ሴክተሩ ተሳትፎ ወሣኝ ሆኖ እያለ መንግሥት በተከተለው የፓርቲ መርህ (Ideology) የግል ሴክተሩ በሀገራችን እንዲጠፋ የተደረገና እንደገና ትክክለኛ ሚናውን እንዲጫወት የተመቻቸ የፖሊሲ ምቹ ሁኔታ ከወረቀት ያለፈ በተግባር ያልተፈጠረ መሆኑ፤
- የቴክኖሎጂ ሽግግር በዘርፉ በተፈለገው ደረጃ ያለመሆን ለምሳሌ የግብዓት አጠቃቀም፣ የመስኖ አጠቃቀምና የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀም፤
- የግብርና ዘርፍ ለኢኮኖሚው ያለውን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ያስገባ የገንዘብ አቅርቦትና አጠቃላይ ኢንቨስትመንት በሴክተሩ ያለመኖር፤
- የዘርፉን ተቋማዊ ችግር በተመለከተ ባልተጠና መዋቅር በየጊዜው የሚቀያየር (frequent restructuring) መሆኑ፣ ዘርፉ በአብዛኛው የግብርና እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች የማይመራና በፖለቲካ ካድሬዎች ተፅዕኖ ስር የወደቀ መሆኑ፣ ሥራዎችን በተጠና ዕቅድ ከመሥራት ፋንታ በዘመቻና የዕለት ዕለት ደራሽ ሥራዎች የተተበተበ በመሆኑ የሚጠበቅበትን ተልዕኮ ማሳካት ያለመቻሉ፤
- ዘርፉን የሚመራው ሚኒስትር መ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት አስመልክቶ በአብዛኛው ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አላማ ላይ የተንጠለጠለና ገበያ ተኮር ያልሆነ ማለትም ከማምረት እስከ ፍጆታ ድረስ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያልፈታ መሆኑ፤
- በግብርና እና ተያያዥ ሙያዎች ሰፊ እውቀትና ልምድ ያላቸው ምሁራን በዘርፉ ጉዳይ ላይ እንዲገለሉ በማድረግ በምትኩ እውቀትና ልምድ በሌላቸው የለብለብ ካድሬዎች እንዲሰራ መደረጉ፤
- በዘርፉ ያሉትን የመንግሥትና ሕዝባዊ ተቋማት፣ የግል ዘርፍ የልማት አጋሮችና መያድ እንዲሁም አለም አቀፍ የግብርና ምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጨምሮ የተቀናጀና ብቁ የማስተባበሪያ ሥርዓት ያለመኖር፤

በአጠቃላይ ዘርፉ ያለበት ሁኔታ ሲታይ መንግሥት ግብርናን እንደ ወሳኝና ትኩረት አቅጣጫ አድርጐ መውሰዱ በጠንካራ ጐኑ የሚታይ ቢሆንም በአተገባበር፣ በበጀት፣ በተቋም አደረጃጀት እና ጥራት ያለው የሰው ኃይል አመዳደብ ደካማ አፈጻጸም ነበረው፡፡

የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት የተቀመጡ

## የኢዜማ የፖሊሲ አቅጣጫዎች

ከላይ የተገለጹትን አንኳር የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት የሚከተሉትን የፖሊሲ እና ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች መከተል ያስፈልጋል

1) ገበያ መር፣ የተቀናጀ፣ ሁሉን አቀፍ የሆነና ሥነ ምህዳርንና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን እና መስኖን መሠረት አድርጐ ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምር የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲን ያራምዳል፡፡ - ይህንንም ለመፈፀም ይቻል ዘንድ እስካሁን የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈና የምርምር ግኝቶችን በግብዓትነት በመጠቀም በየጊዜው ክለሳ ያደርጋል፡፡

2) የመሬት ፖሊሲን በተመለከተ፡ - በሕዝብ ውይይትና ፈቃደኝነት ላይ በመመስረት የግል፣ የመንግሥትና የማህበረሰብ የመሬት ባለቤትነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ መሬት ከአንድ የመሬት ባለቤት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን በሽያጭ፣ በኪራይ፣ ወዘተ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡ መሬት ለሃገር ልማት ቁልፍ ሀብት በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመሬት ፖሊሲ በማውጣት የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሴክተሩም ከተበታተነ መስሪያቤቶች ሀላፊነት ተሰብስቦ በአንድ መ/ቤት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

3) በሀገሪቱ የማምረት አቅም ያላቸውን አካባቢዎች በመለየት በተመረጡ የግብርና ምርቶች (ሰብሎች፣ ተፈጥሮ ሀብቶች እና የእንስሳት ሀብት) ላይ በማተኮር ከፍተኛ ግብዓቶችን (መስኖ የተሻሻሉ ዝርያዎች፣ ባዮቴክኖሎጂ መካናይዜሽን፣ ወዘተ) እና የአሠራር ዘዴዎች በመጠቀም በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ በማምረት ምርት እና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር በምግብ ራስን መቻልና ከውጭ የሚገባውን ምግብ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት (food security & Import substitutions) እንዲቻል ይደረጋል፡፡

4) በዘርፉ የግል ሴክተሩ ሚና የማይተካ በመሆኑ የሥራው ባለቤት የሚሆንበትን ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት የግል ሴክተሩ የተለያዩ የግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት በመስጠት በግብርና ምርት

ማምረትና ግብይት ላይ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የመንግሥት ሚና በተመለከተ ለግሉ ሴክተር አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ ደረጃዎችን በማውጣትና ቁጥጥር በማድረግ የግሉ ዘርፍ ለጊዜው ሊገባባቸው በማይችሉ ተግባራት ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

5) ግብርናን መሠረት ያደረጉ የገጠር ከተሞች እንዲፈጠሩ በማድረግ፣ የከተማ ግብርናን እና ደን ልማትን በማስፋፋት፣ ትናንሽና መካከለኛ አግሮ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ቀላል ኢንዱስትሪዎችን እንዲስፋፉ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር የወጣት ኃይሉን ሥራ በማስያዝ ለክፍለ ኢኮኖሚው አስተዋጽኦ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

6) ገበሬዎችና አርብቶአደሮች ችግሮቻቸውን ፈተው ፍላጐቶቻቸውን በጋራ ለማሳካት ይችሉ ዘንድ በነፃ ፍላጐት ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ማህበራት ከማንኛውም ያልተገባ ተፅዕኖ ውጭ በሆነ መንገድ እንዲደራጁ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

7) የግብርና ምርምሩን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት አሳታፊ እና ችግር ፈቺ የሆነ ምርምር እንዲስፋፋ ማድረግና የግብርና ምርምርና ውጤቶችንም ከግል ሴክተሩ እና ከግብርና ኤክስቴንሽን እንዲሁም ትምህርት ተቋማት ጋር ተሳስረው እንዲሄዱ ከማድረግ አኳያ አጠቃላይ አሰራራቸው እና አደረጃጀታቸው ተፈትሾ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

8) ተፈጥሮ ሀብታችንን (ውኃ፣ ደን፣ ዱር እንስሳት፣ አፈር፣ ብዝሀ ሕይወት ወዘተ...) ለሀገራችን ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ዝርዝር ስትራቴጂ እና የድርጊት መርሀግብር እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡ በመነሻነት፡-

- አሁን ያለውን ከፍተኛ የሆነ የአፈር ብክለትና ለምነት መታጣት ለመቀነስ እስካሁን ይካሄዱ የነበረው የዘመቻ ሥራ በመለወጥ በሙያ በታገዘና ጥራቱን በጠበቀ ቴክኖሎጂዎች ሥነ ምህዳርንና ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የአፈር ጥበቃ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡
- የውኃ ሀብቶቻችንን (ከርሰ ምድርና ገፀ ምድር) በአግባቡ በመሰብሰብ፣ በመጠበቅና በመጠቀም የግብርናና ገጠር ልማቱ እንዲሳለጥ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከዚህ ቀደም የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመገምገም እንዲከለሱ ይደረጋል፡፡
- በደን ሀብቶቻችን ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በማካሄድ የሀገሪቱን የደን ሽፋን በማሳደግ ንዑስ ሴክተሩ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያለው ጉልህ ሚና እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ይህንንም ለማስፈፀም ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
- የዱር እንስሳት ሀብቶቻችንን እና መጠለያ ቦታዎቻቸውን ሕብረተሰቡን ባሳተፈ እና ተጠቃሚ ባደረገ ሁኔታ በተገቢው መንገድ በመጠበቅ በመንከባከብና ጥቅም ላይ በማዋል፣ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በመመደብ እና አግባብነት ያለው ተቋም በማቋቋም ከዘርፉ የሚገኘውን የቱሪዝም እና ሌሎች ገቢዎች ከፍ እንዲሉ ይደረጋል፡፡

9) ሴቶች በግብርና ዘርፍ አስተዋጿቸው የጐላ ቢሆንም ተጠቃሚነታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ይህን ለማሻሻል ሥነ-ፆታን ታሳቢ የሚያደርጉ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞችን በመንደፍ ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

10) በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውስጥ የሥነ ምግብ ችግሮችን የሚፈታ አደረጃጀትና የቴክኖሎጂ ፓኬጅ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

11) የግብርናው ዘርፍ እድገት ለማፋጠን የገጠር መሠረተ ልማቶችን ማለትም የገጠር መንገድ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ ሙብራት፣ የመጠጥ ውኃ እና የመረጃ መረብ ስርዓት (ICT) ወዘተ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

12) ለዝናብ አጠር እና አርብቶ አደር አካባቢዎች ካሉባቸው የተለዩ ችግሮች አኳያ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችና የተቀናጁ የልማት ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ተቀርፀው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

13) የግብርና ዘርፍን የሚመራው መዋቅር የታለመውን የግብርና ፖሊሲ ሊያሳካ በሚችል መልኩ እንደገና በጥናት ተመስርቶ ይደራጃል፣ ብቃት ባለው ባለሙያ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ምርምር፣ የግብርና ኤክስቴንሽንና ገበሬዎች እና ሌሎች አጋር አካላትን አቀናጅቶ የሚያስተባብር ጠንካራ ተቋማዊ ሥርዓት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶች

1. በአጭር ጊዜ ውስጥ በመስኖ በመታገዝ ምርታማነትን በመጨመር በምግብ እህል ራስን መቻል (self-sufficiency) ከውጭ የሚገቡትን የምግብ ውጤቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ይሆናል፡፡
2. በመካከለኛ ጊዜ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ሙሉ በሙሉ መሸፈን እንዲሁም ለወጪ ገበያ የሚሆኑ ምርቶችን በብዛትና በጥራት አምርቶ ለመላክ ማስቻል ይሆናል፡፡
3. በረዥሙ ጊዜ ደግሞ በግብርና ዘርፍ ሙሉ በሙሉ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ይሆናል፡፡

## የግብርና ዘርፉ ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

የግብርናና ገጠር ልማትና እድገት ለማፋጠን በዘርፉ ውስጥ በቀጥታ ከሚሠሩ ሥራዎች ውጭ ዘርፉን የሚያግዙና አልፎ ተርፎም ምርቶቹን ተቀባይ የሆኑ ሌሎች ዘርፎች ስላሉ ከነዚህ ዘርፎች ጋር ተቀናጅቶና ተጋግዞ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን የሚያስተባብር በጠ/ሚ የሚመራ አንድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይቋቋማል።

# ኢዜማ በዋሽንግተን ዲሲ የከተማ ቻፕተር ምርጫ አካሄደ

መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜናች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የዋሺንግተን ዲሲ የከተማ ቻፕተር መስራች ጉባኤ እሁድ መስከረም 18 ቀን 2012 ዓ.ም መካሄዱን የኢዜማ ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገለፁ።

በእለቱ፣ በአሜሪካን ሀገር የሥራ ጉብኝት እያደረጉ የሚገኙት የፓርቲው ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌ በጉባኤው ላይ በመገኘት የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል። የዓለምአቀፍ የድጋፍ ማኅበር አስተባባሪ ድርጅት አባል የሆኑት ታምራት ወርቁ ስለ ድጋፍ ማኅበሩ ዓላማና አመሰራረት ሂደት መግለጫ የሰጡ ሲሆን ከተሳታፊዎች ለቀረቡ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ምላሽ ሰጥተዋል። ከጥያቄና መልሱ በማስከተል የአባላት ምዝገባ የተካሄደ ሲሆን ከአባላት መካከል ሦስት ሰዎች ባስመራጭነት ተሰይመው የአመራር እና የተወካዮች ምርጫ ተካሄዷል።

ማኅበሩን ለመመስረትና ምርጫ ለማካሄድ የሚያስፈልገው የአባላት ቁጥር ተሟልቶ በተካሄደው ምርጫ፣ አምስት አባላት ያሉበት የዋሽንግተን ሜትሮ አካባቢ የኢዜማ ድጋፍ ማኅበር አመራሮችና ከተማውን ወክለው ለዓለምአቀፍና ለአህጉር ተወካዮች የሚሆኑ ሦስት አባላት ተመርጠዋል። በዚህም መሰረት ሾላ አውግቸው፣ ካሌብ ሽፈራው፣ እውነት ጌታሁን፣ ጣሰው መልካሕይወት እና ሳሙኤል ደጋጋ ለከተማ ኮሚቴ አመራርነት የተመረጡ ሲሆን ኤልሳቤጥ ጌታቸው፣ መሳይ ዘርጋ እና ታምራት ወርቁ ለክፍለ ዓለማትና ዓለም አቀፍ ኮሚቴዎች የተመረጡ መሆናቸውን ለዜጎች መድረክ የደረሰው መረጃ ያስረዳል።

# ኢዜማ በሰሜን ሸዋና በኮምቦልቻ ህዝባዊ ውይይት ሊያካሄድ መሆኑ ታወቀ

መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሰሜን ሸዋና በኮምቦልቻ ሕዝባዊ ውይይት ሊያካሂድ መሆኑን የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ገለጹ፡፡
ኢዜማ በሰሜን ሸዋ ጥቅምት 2 ቀን 2012 ዓ.ም በእነዋሪ አይሲቲ አዳራሽ፣ በደነባ ደግሞ በወረዳው በሚገኘው ወጣት ማዕከል ውስጥ ውይይት ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም መስከረም 25 ቀን 2012 ዓ.ም በኮምቦልቻ ከተማ በተመሳሳይ መልኩ ሕዝባዊ ውይይት እንደሚያደርግ ታውቋል፡፡
በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ከማኅበረሰቡ ጋር በቅርበት በመወያየት በተጨባጭ ያሉትን ችግሮች ለመረዳት እና የኢዜማን ግቦች እና የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ለማስተዋወቅ የሚካሄዱት ተከታታይ ሕዝባዊ ውይይቶች አካል የሆነው የሦስቱ ከተማዎች ውይይት በአካባቢው የኢዜማ የምርጫ ወረዳ መዋቅሮች የተዘጋጁ ናቸው፡፡
ከሕዝባዊ ስብሰባው በፊት በወረዳው የሚገኙ የኢዜማ አባሎችና አመራሮች ስብሰባው በሚካሄድበት አካባቢ ለሁለት ቀናት ቅስቀሳ እንደሚያደርጉ፣ በተመሳሳይም የፓርቲውን አላማና ፕሮግራም የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሠሩ ታውቋል፡፡

## ኢዜማ ከሴታዊት ንቅናቄ አባላትና አመራሮች ጋር ተወያየ

መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



ፎቶ ክሬዲት፡- ከሴታዊት ንቅናቄ ማሕበራዊ ድህረ ገፅ የተወሰደ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ማክሰኞ መስከረም 20 ቀን 2012 ዓ.ም ከሴታዊት ንቅናቄ አባላት ጋር ውይይት ማድረጉን የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ከውሰር እድሪስ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡
ሴታዊት ንቅናቄ በኢትዮጵያ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ የሚሠሩ ሴቶች ንቅናቄ ሲሆን ከተቋሙ ጋር በነበረው ውይይት የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ የሆኑት ከውሰር እድሪስ እና ናንሲ ውድነሕ እንዲሁም የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ተገኝተው ነበር፡፡ ከሴታዊት ንቅናቄ አመራር አባላት ጋር በተደረገው ውይይት ኢዜማን ሊያግዙ ከስምምነት ላይ እንደተደረሰ ከውሰር እድሪስ ገልፀዋል፡፡

በሴቶች ጉዳይ ሥር የጥናትና ዶክመንቴሽን ንዑስ መምሪያ፣ የአቅም ግንባታ ንዑስ መምሪያ እና የፖሊሲና ስትራቴጂ ንዑስ መምሪያዎች እንዳሉ የጠቆሙት ተጠሪዋ እነዚህን መምሪያዎች በሥርዓተ-ፆታ ባለሙያዎች መደገፍ ስለሚያስፈልግ ንቅናቄው ድጋፍ ሊያደርግ እንዲሁም የሴቶችን አቅም ለማጎልበት የአመራርነት ሥልጠና ለመስጠትም ከስምምነት ላይ መደረሱን አስረድተዋል፡፡

ከፖለቲካ ፓርቲዎች ለሴታዊት ንቅናቄ በሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ላይ በጋራ የመሥራት ጥሪ ሲቀርብ የኢዜማ ጥያቄ የመጀመሪያው መሆኑን በሴታዊት ንቅናቄ በኩል እንደተገለፀላቸው ተጠሪዋ ገልፀዋል፡፡

«ፓርቲያችን ኢትዮጵያን ዘመናዊ ማድረግ ነው ራዕዩ፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ 50 በመቶ ያህል ሴቶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ሴቶችን በመተው ኢትዮጵያ ማዘመን አይቻልም፡፡ ሴቶች ወደ ፖለቲካ እንዳይመጡ የሚያደርገውን ገፊ ምክንያቶች አጥንቶ መፍትሔ መስጠት ግድ ይላል፡፡» ብለዋል ተጠሪዋ፡፡